# ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበውን የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 144/2011

መጋቢት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 144/2011

ማንኛውም ታክስ ከፋይ እራሱ አስልቶ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ የታክስ ባለሥልጣኑ ሲፈቅድለት ሊያሻሽል እንደሚችል በአዋጁ የተደነገገ በመሆኑ እና፤

የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለማሻሻል በታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ሲቀርብ ማሻሻያው ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ግልጽ አሰራር ማስቀመጥ በማስፈለጉ፣

ሚኒስትሩ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 29(3) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 144/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ፡

1/ "**የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማሻሻል**" ማለት ታክስ ከፋዩ በራሱ ውሳኔ መጀመሪያ ባቀረበው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ የተገለፀውን የታክስ መጠን በመጨመር ወይም በመቀነስ ወይም ሌላ ለውጥ በማድረግ የሚያቀርበው ማሻሻያ ነው፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

2/ "**ቦርድ**" ማለት በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎች ድንጋጌ መሠረት የውጭ ኦዲተሮች የሚያዘጋጁትን የሂሳብ ሪፖርት መርምሮ ማረጋገጫ የሚሰጥ የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ ኦዲት ቦርድ ነው፡፡

3/ **"የታክስ ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ገቢዎች ባለሥልጣን እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለሥልጣን ማለት ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውንም ይጨምራል፡፡

4/ "**ሚኒስቴር**" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን የሚኒስቴሩን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይጨምራል፡፡

5/ "**ሚኒስትር**" ማለት የገቢዎች ሚኒስትር ነው፡፡

6/ **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

7/ **"ደንብ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009 ነው፡፡

8/ በዚህ አንቀፅ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

9/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 3. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ የራስ ታክስ ስሌት በሚያቀርብ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

* በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ... * Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

4. <u>የታክስ ስሌት የሚሻሻልበት ምክንያት</u>

1/ ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት እንዲሻሻልለት ሲያመለክት በሚከተሉት ምክንያቶች ሚኒስቴሩ ሊያሻሽልለት ይችላል፡፡

ሀ) የድምር ስህተት ሲኖር፤

ለ) የአፃፃፍ ስህተት ሲያጋጥም፤

ሐ) ከሒሳብ መደብ አመራረጥ (Chart of Account) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲኖር፤

መ) የጆርናል ምዝገባ ስህተት ሲኖር፤

ሠ) ሂሳብ ወደ ሌጀር ሲተላለፍ የተከሰተ ስህተት ሲያጋጥም፤

ረ) ከሒሳብ ማስተካከያ (Adjusting Entry) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲያጋጥም፤

ሰ) በሒሳብ መዘገብ ላይ ሳይመዘገብ የተዘለለ የገቢና ወጪ ሰነድ ሲኖር፤

ሸ) የመጀመሪያ ወይም የመጨረሻ ሀብት ቆጠራ አያያዝ ስህተት ሲኖር፤

ቀ) የሒሳብ አያያዝ ዘዴ ስህተት ሲያጋጥም፤

በ) በታክስ ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የውጭ ኦዲተሮችን የኦዲት ሪፖርት ሲመረምር ባገኘው ግኝት መሠረት የሚደረግ ማስተካከያ ሲያጋጥም፤

ተ) ሦስተኛ ወገን በሚሰጠው ማረጋገጫ ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት በሂሳብ መዝገቡ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ሲያስፈልግ፣

ቸ) በታክስ ሕግ ያልተፈቀደ ወጪ በተቀናሽነት በመያዙ ምክንያት የተፈጠረ ስህተት ሲኖር፤

ኀ) የግልና የንግድ ሒሳቦች በመቀላቀላቸው የተፈጠረ ስህተት ሲያጋጥም፤

ነ) በታክስ ማስታወቂያ ቅፅ ላይ የአመዘጋገብ ወይም የአገላለጽ ስህተት ሲያጋጥም፣

ኘ) በታክስ ወይም በተለይ በኤክሳይዝ ታክስ ሂሳብ አያያዝ ላይ የማምረቻና አስተዳደራዊ ወጪዎች ተፋልሰውና ባልተገባ ቦታ ላይ ተመዝግበው ሲገኙ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች የተለየ እና በሚከፈለው የታክስ መጠን ላይ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል አሳማኝ ምክንያት ሲያጋጥም ስራ አስኪያጁ የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## 5. የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል የሚቀርብ ማመልከቻ

1/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻልለት በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ የታክስ ስሌቱን ለማሻሻል ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በዝርዝር መጥቀስ አለበት፡፡

2/ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ማልከቻው ከቀረበበት ቀን በፊት ባሉ 5 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በነበሩ የራስ ታክስ ስሌቶች ላይ ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ የሁሉም ዘመናት የታክስ ስሌት ማሻሻያ በአንድነት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 6. የማመልከቻው ይዘት

1/ በራስ ታክስ ስሌት ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ የሚቀርበው ማመልከቻ ለውጡን የሚያሳይ ሆኖ የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፡፡

(ሀ) የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ የተጠየቀበትን የታክስ ጊዜ እና ዓይነት፤

(ለ) ማሻሻያ የሚደረግበትን ጉዳይ እና ምክንያቱን ፣

(ሐ) ማሻሻያ እንዲደረግበት የተጠየቀው ጉዳይ የሚያስከተለው የገንዘብ ወይም ሌላ ለውጥ፣

(መ) በሚሻሻለው የታክስ ስሌት የተገለፀው የታክስ መጠን ወይም ወደፊት የሚሸጋገር ኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለ የግብዓት መጠን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

2/ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል የሚቀርበው ማመልከቻ ከማሻሻያ ምክንያቶቹ ጋር አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

## 7. <u>ማመልከቻው የሚቀርብበት ጊዜ</u>

1/ ታክስ ከፋዩ የራስ የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ለሚኒስቴሩ የሚያቀርበው ማመልከቻ የራስ የታክስ ስሌቱን ማስታወቂያ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግበት የሚቀርብለትን ማመልከቻ ተቀብሎ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ባሉት አንድ መቶ ሃያ ቀናት ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ የቀረበለትን የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ተቀብሎ ማሻሻያው እንዲደረግ ወይም ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ሊወስን ይችላል፡፡

## 8. የውሳኔ አሰጣጥ

ሚኒስቴሩ፡-

1/ በቀረበለት ማመልከቻ መሰረት የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ የፈቀደ እንደሆነ የታክስ ስሌቱን በማሻሻል ለታክስ ከፋዩ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ይልክለታል፡፡

2/ የቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ በጽሁፍ ለታክስ ከፋዩ ያሳውቀዋል፡፡

## 9. የተሻሻለ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በድጋሚ ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ታክስ ከፋዩ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል ወስኖ የተሻሻለውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 28 መሠረት ለታክስ ከፋዩ የተሻሻለ የታክስ ሰሌት ማስታወቂያ ከመስጠት አያግደውም፡፡

## 10. የታክስ ስሌት ማሻሻያ የሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

1/ ሚኒስቴሩ የመጀመሪያ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ(official assessment notice) ከሰጠ በኋላ ወይም ኦዲት በመደረግ ሂደት ላይ የሚገኝ ከሆነ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ (amendment of self assessment) ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2/ አንድ ጊዜ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበት የራስ ታክስ ስሌት በድጋሚ ማሻሻያ እንዲደረግበት ጥያቄ ሊቀርብበት አይችልም፡፡



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

3/ በግብር ዘመኑ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የተመደበ ታክስ ከፋይ የሚያቀርበው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተው ቢኖርም ሚኒስቴሩ በራሱ አነሳሽነት የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 11. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ -----/ 2011 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ
የገቢዎች ሚኒስቴር
ሚኒስትር